# UW Medicine

## የፋይናንስ እርዳታ ፖሊሲ – በግልጽ ቋንቋ የተጻፈ አጭር ዝርዝር

የሚሰጠው የገንዘብ እርዳታ፡ UW Medicine ባለው የፋይናንስ እርዳታ ፖሊሲ መሠረት፣ ለድንገተኛ ሕክምና ወይም ለሌላ በሕክምና አስፈላጊ ለሆነ እንክብካቤ መክፈል ለማይችሉ ብቁ ታካሚዎች የፋይናንስ እርዳታ ይሰጣል። የ UW Medicine ን የሚመርጡ ታካሚዎች፣ ካለን ልምድ፣ ሞያና ባለው በጣም ዘመናዊ በሆነው የሕክምና እንክብካቤ፣ ሁሉንም ባንድ የጤና ጥበቃ ጥላ ሥር ማግኘት ይችላሉ። “UW Medicine”፣ የሚከተሉትን Airlift Northwest, Harborview የህክምና ማዕከል ፣ UW የህክምና ማዕከል ፣ Northwest ሆስፒታል እና የህክምና ማዕከል ፣ UW ሐኪሞች፣ UW የአጎራባች ክሊኒኮች፣ እና Valley የህክምና ማዕከልን ያካተተ ነው።

የብቁነት መስፈርቶች እና የቀረበው ድጋፍ፡ ለገንዘብ እርዳታ ብቁ መሆን በበርካታ ሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ ነው። እነዚህም የሚፈለገው እንክብካቤ አይነት፣ የኢንሹራንስ(መድህን) ሽፋን ወይም ሌላ የክፍያ ምንጭ፣ገቢ፣የቤተሰብ መጠን፣ንብረት፣የዋሽንግቶን ስቴት ነዋሪነት፣ ታካሚው ወይም ሃኪሙ ሊጠቃለል ይገባል የሚሉት ልዩ ትኩረት።

የፋይናንስ እርዳታ የሚጠይቁ ታካሚዎች የሚከተሉትንም ጨምሮ የፋይናንስ እርዳታ ማመልከቻ ሂደትን መከተል አለባቸው፣ ከሚከተሉት ውስጥ አንዱን የ W-2 መግለጫ፣ ወቅታዊ የደሞዝ ቼክ ቀሪ ቁራጮች፣ የባንክ ሂሳብ መግለጫ ወይም ላለፈው ዓመት የገቢ ግብር ሰነድ ማቅረብ፣ እንዲሁም ሊኖሩ ስለሚችሉ ሁሉም የፋይናንስ እርዳታ ምንጮች ማመልከቻን መሟላት አለባቸው፣ እንደ Medicaid የመሳሰሉትን በመንግስት የሚደጎሙ እርዳታዎችንም ጨምሮ።

ለእርዳታ እንዴት ማመልከት እንደሚቻል፡ ታካሚው ወይም ማንኛውም በታካሚው እንክብካቤ የሚያገባው ሰው፣ የቤተሰብ አባልና አገልግሎት ሰጪውን ጨምሮ በማንኛውም ሰአት ሰለታካሚው የገንዘብ ችግር ማንሳት ይችላሉ። ታካሚው ወይም ኃላፊነት ያለበት ወገን የፋይናንስ እርዳታ ማመልከቻ እንዲሞላ ይበረታታል። ለፋይናንስ እርዳታ ብቁ ለመሆን፣ ለሒሳቡ የፍርድ ቤት ትዛዝ ከመደረሱ በፊት በማንኛውም ግዜ ላይ ማመልከቻ ማስገባት ይቻላል።

የፋይናንስ እርዳታው የሚወሰነው በ UW Medicine ቦታዎች በ UW የሕክምና ባልደረቦች ለተሰጡ የሕክምና እንክብካቤዎች ብቻ ነው። እንደ የመጓጓዣ፣ የምግብ፣ የማረፊያ ቦታና ለዘላቂ የሕክምና መሳሪያዎች ወጪዎች የመሳሰሉት በዚህ የፋይናንስ እርዳታ ፖሊሲ ስር አይሸፈኑም።
በሐኪም የታዘዙ መድሃኒቶች በ UW Medicine በኩል ታዘው በ UW Medicine ፋርማሲ (ካለ) ከተሞሉ ሽፋን ይደረግላቸዋል። UW Medicine ፣ የእያንዳንዱን ታካሚ ምስጥርና ክርብ ይጠብቃል። በ Health Insurance Portability and Accountability Act (HIPAA) መሠረት ለፋይናንስ እርዳታ የሚቀርብ ማንኛውም መረጃ፣ እንደ የተጠበቀ የጤና መረጃ ሆኖ ይቆጠራል።

ግልባጮችንና መገናኛ መረጃን የት ማግኘት እንደሚቻል፡ የUW Medicine የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ፣ የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ፣ በግልጽ ቋንቋ የተጻፈ አጭር ዝርዝር፣ እና የሂሳብ አከፋፈል እና ስብስብ መመሪያዎች ያለክፍያ በነጻ ማግኘት ይቻላል። እነዚህን ሰነዶች በተለያዩ ቋንቋዎች በኢንተርኔት፣ በስልክ ወይም በአካል ተገኝተው ማግኘት ይችላሉ። ሰነዶችን ከሚከተሉት ድረገጾች ዳውንሎድና ፕሪንት ማድረግ ይችላሉ www.uwmedicine.org/financialassistance ወይም www.valleymed.org/financialassistance. እንክብካቤ የሚፈልጉበትን ቦታ በመጥራት ቅጂዎን መጠየቅ ይችላሉ ። ግልባጮቹን በአካል፣ በ UW Medicine የሐኪም ቤት ቦታዎች ውስጥ ባሉ የታካሚ መቀበያዎች እና የድንገተኛ ሕክምና ክፍል (Admissions and Emergency Departments) ውስጥ ይገኛ

| | | |
|---|---|---|
| **Harborview Medical Center**<br>Financial Counseling<br>325 9th Ave; Mail Stop 359758<br>Seattle, WA 98104-2499<br>206.744.3084<br>ፋክስ 206.744.5187<br>ሰ-ዓ 8:00 a.m. – 4:30 p.m. | **Medical Center-Montlake**<br>Financial Counseling<br>1959 NE Pacific Street Mail Stop 356142<br>Seattle, WA 98195-6142<br>206.744.3084<br>ፋክስ 206.598.1122<br>ሰ-ዓ 8:00 a.m. – 4:30 p.m. | **UW Medical Center-Northwest**<br>Financial Counseling<br>1550 N 115th St<br>Seattle, WA 98133-9733<br>206.744.3084<br>ሰ-ዓ 8:00 a.m. – 4:30 p.m. |
| **Harborview Medical Center**<br>**UW Medical Center**<br>Patient Financial Services<br>10330 Meridian Ave. N Suite 260<br>Seattle, WA 98133<br>206.598.1950 ወይም 1.877.780.1121<br>ፋክስ 206.668.6469<br>ሰ-ዓ 8 a.m. – 4:30 p.m. | **Valley Medical Center**<br>Patient Financial Services<br>3600 Lind Ave SW, Suite 110<br>Renton, WA 98057-4970<br>425.690.3578<br>ፋክስ 425.690.9578<br>ሰ-ዓ 8:00 a.m. – 5:00 p.m. | **UW Physicians**<br>**UW Neighborhood Clinics**<br>Patient Accounts & Inquiry<br>P.O. Box 50095<br>Seattle, WA 98145-5095<br>206.520.9300 ወይም 1.855.520.9300<br>ፋክስ 206.520.3200<br>ሰ-ዓ 9:00 a.m. – 5:00 p.m. |
| **Harborview Medical Center**<br>**UW Medical Center**<br>Patient Financial Services<br>P.O. Box 95459<br>Seattle, WA 98145-2459<br>206.598.1950 ወይም 1.877.780.1121<br>ፋክስ 206.598.2360<br>ሰ-ዓ 8:00 a.m. – 4:30 p.m. | **Valley Medical Center**<br>Patient Financial Services<br>P.O. Box 59148<br>Renton, WA 98058-2148<br>425.690.3578<br>ፋክስ 425.690.9578<br>ሰ-ዓ 8:00 a.m. – 5:00 p.m. | **Airlift Northwest**<br>Patient Financial Svs<br>6505 Perimeter Road S., Ste 200<br>Seattle, WA 98108<br>206.598.2912<br>ፋክስ 206.521.1612<br>ሰ-ዓ 8:00 a.m. – 5:00 p.m. |